# የጥምቀት በዓል

## (የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ጥምቀት በዓል በኢትዮጵያውን እይታ)

"ይደልወነ ንፈጽም ኩሎ ጽድቀ"

"ጽድቅን ሁሉ መፈጸም ይገባናል" (ማቴ ፫፡፲፬_፲፯)

ቀሲስ አስተርአየ ጽጌ

nigatuasteraye@gmail.com

ጥር ፩ ፳፻፮ ዓ.ም.

# መግቢያ

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዮርዳኖስ ውሀ በዮሐንስ እጅ እንደተጠመቀ እንኳን ክርስቲያን ከክርስትና እምነት ውጭ የሆነ ሁሉ ያውቀዋል። ክርስቲያን ነኝ የሚል ሁሉ ይሰብከዋል። በተለይ እኛ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ካህናት የጥንት ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት አበው በሰሩልን ስርአት ከዓለም ልዩ በሆነ መንገድ እናንጸባርቀዋለን። በውስጡ ያዘለው ለወዳጅ ለጠላት የተሸከመው የመልእክቱ ይዘት እና ጥልቀት ምን ያህል እንደገባን እራሳችንን እንጠይቅ። ምክንያቱም ይህች ጦማር የተሸከመችውን ያባቶቻችንን ስሜት ለመናገር ለመመስከርና ትውልዱን ለማስተምር የሚጠይቅና የሚፈትን ከዚህ ዘመን የከፋ የለም።

ስለ ጥምቀት በዓል ሁሉም የሚሰብከውን ሁሉም የሚያውቀውን በዚህች ጦማር ገልብጬና መልሸ በመናገር አንባቢን ማድከም አልፈልግም። ሲነገር ብሰማ ኖሮ ሰአቴን ባላጠፋሁ እኔም ባልደከምኩ ነበር። ይህ አባቶች በውስጤ ያስቀመጡት ዛሬ በኢትዮጵያ ላይ ሲደረግ ከማየውና ከምሰማው ጋራ በመጋጨት ስሜቴን የጦር ሜዳ አድርጎ ገንፍሎ የወጣ ነው።

# ኢትዮጵያውያን የሚባሉት እነማናቸው?

በኢትዮጵያውያን እይታ ብየ ስላቀረብኩት፤ ኢትዮጵያውያን የሚባሉት እነማናቸው? በጥምቀት ላይ ያለውን የትኛውን ጎሳ እይታ ነው የማቀርበው? ስለዚህ መጀመሪያ ይህ ጥያቄ መመለስ ያለበት ይመስለኛል።

ክፉ ነገር ላደረገ እድሜ መመኘት ለንስሀ ካልሆነ በቀር ባለበት እንዲቆይ እድሜ  ለሱ አይባልም። ስለዚህ የወያኔን እድሜ ያሳጥረውና ኢትዮጵያ የምትባል አገር የለችም ብትኖርም ካጼ ምንይልክ ወዲህ ነው በሚለው ስብከቱ ኢትዮጵያዊነታቸውን የካዱ የዜግነት ህብረታቸውን የናዱ ስላሉ የኢትዮጵያዊነትን ማንነትና ምንነት ሳንረዳ ወደ ጥምቀቱ እይታ መሻገሩ የጽሑፉን መሰረት ያሳጣዋል።

ኢትዮጵያዊ የሚባለው የየትኛው ጎሳ አካል ነው? ከኢትዮጵያውያን ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት የራሳቸውን ዝንጉርጉርነት ነቢዩ ኤርምያስ በተናገረው ሲገልጹት እንደ ሰማሁት ኢትዮጵያዊነት የቀለሞች  የቋንቋዎች፤ የእምነቶች እና የጎሳዎች ዝጉርጉርነት ውጤት ነው። ከዚህ በታች በሰፈረው ሀሳብ ኢትዮጵያዊነትን ሊቃውንት እንዲህ ይገልጹታል።

ከክርስትና በፊት አክሱም በሩቅ በምትፈልቅበት ዘመን ከሩቅ እና ከመካከለኛው  ከሩቅ ምስራቅ እንዲሁም ከሚያዋስኗት አገሮች ከተለያዩ የሰው ዘሮች ብዙ ሰው ገብቶባታል። በነበራት የንግድ የፖለቲካ እና የባህል እንቅስቃሴ ህዝቡ እየተካካበና እየተሳሰረ እስከ  ዘመነ ዮዲት ደረሰ።

በስምንተኛው ክፍለ ዘመን ዮዲት ከተማዋን እንዳልነበረች ስታደርጋት ህዝቡ ቀይ ባህርን ተሻግሮ ወደ መጣበት አልተመለሰም። ወደ መሀል አገር ገብቶ ተበትኗል። ደንብሮ የወጣ ህዝብ ባረፈበት እየሰፈረ ካካባቢው ጋራ እራሱን እያስማማ እስከ ዘመነ ግራኝ ወረራ ደረሰ።

ግራኝ መሀመድ ከምሥራቅ ተነስቶ የምስራቁን ህዝብ ሰራዊት አድርጎ አገሪቱን በወረረ ጊዜ ከሱ ጋራ የዘመተው እስከ ሰሜኑ ጫፍ ድረስ ዘልቆ በመሄድ በየደረሰበት ንብረት እያፈራ መኖር ጀመረ። ወደ ተነሳበት መንደሩ አልተመለሰም።

ይህም ብቻ አይደለም በዘመነ መሳፍንት በነበረው ትንቅንቅ አንዱ ሌላውን አሸንፎ  ለማስገበር ሲል በፈጸመው የእርስ በርስ ወረራ፤ በኢትዮጵያ ምድር ባለው በማነኛውም ጎሳ ባይሆን እንኳ ጡት መቁረጥ እንጅ ሴት መግደል ነውር ስለነበረ፤ የአራዊት ባህርያት ጎልተው በታዩባቸው ወቅቶች ኦረሞው ባማራው ላይ ሲዘምት ወንዱን እየገደለ ሴቱን እየማረከ በመውሰድ የማረካቸውን ፯ ስድስቱ ሴቶች ለቆሮዎችና ለጄሌዎቻቸው በማሰራጨት ያድሉ ነበር።

አማራውም በለስ ሲቀናው ጡት አይቁረጥ አይስለብ እንጅ ግድያንና ማሰቃየትን እየተጠቀመ ሴት የመግደልን ነውርነት አክብሮ  የማረካቸውን  ፯ ስድስቱን ሴቶች ለጎበዝ አለቃው ለጭቃ ሹሙ እቁባት እያደረገ ይረጭ ነበር። ከዚያም በኋል እስከ ወያኔ ዘመን ድረስ የነበረው የኢትዮጵያ ህዝብ ከቤተ መንግስት ጀምሮ በራሱ ፈቃድ እየተዋደደ እና እየተፋቀረ በመጋባት ካሳለፈው ህይወት የመነጨ የተወሳሰበ (ወሲብ) ህዝብ ነው።

*በነገራችን ላይ ወሲብ በስምምነት በህግ በጋብቻ በፍቅር ለሚፈጸም ሩካቤ ሥጋ እንጅ የሴቷን ፈቃድ ሰብሮ ና ገስሶ ለሚፈጸም ገላጭ ሆኖ የሚሰጥ አይደለም። በዘመናችን ወሲብ የምትባለው ቃል በእንስሳ ባህርይ ለሚፈጸም ሩካቤ ተሰጥታ ወንዶች ሴቶችን አስገድደው ለሚፈጽሙት መግለጫ ተደርጋ ስትነገር ተሰማለች። ካባቶች የሰማሁት ያለ ሴቷ ፈቃድ በወንድ ግዳጅ የሚፈጸመው ሩካቤ ለእንስሳ የምትሰጠው "ስሪያ" የምትለው ቃል ስለሆነች በወሲብ ፋንታ ስሪያ ብትባል ተስማሚ ትመስለኛለች።*

የዚህ ምስቅልቅልና ዝጉርጉር ጎሳ  ውጤት አይደለሁም፤ አይነካኝም የሚል በኢትዮጵያ ተወልዶ ወደ ህልውና የመጣ ሰው ካለ፤ ከግንድ ወይም ከድንጋይ ስር ወይም ከሰማይ ዱብ ያለ ወፍ ዘራሽ የሆነ ሰው ነው። የጥምቀትን በዓል የምናየው በወፍ ዘራሾች እይታ ሳይሆን የኢትዮጵያ ህዝብ በመነጨበት መንገድ መጥቶ በህልውና ላይ ባለው ህዝብ እይታ ነው። ይህ ህዝብ ያለፈባቸውን ሶሶት ህግጋት ፩ኛ ሕገ አራዊትን ፪ኛ ሕገ ኦሪትን ፫ኛ ሕገ ክርስቶስን እንመለከታለን።

# ኢትዮጵያ ያለፈችባቸው ሕግጋቶች

፩ኛ፦ሕገ አራዊት

፪ኛ፦ሕገ ኦሪት

፫ኛ፦ሕገ ክርስቶስ ብለው በሶስት ከፍለውታል።

በሕገ አራዊት ዘመን በሕሊናቸው ዳኝነት ይመሩ የነበሩ ጥቂት ሰዎች ስለተከሰቱ ያ ዘመን ዘመነ—አበው ወይም ሕገ—ልቡና በመባል ይታወቃል። በዓለም ላይ የሚበዛው በህገ አራዊት የሚመራው ስለነበረ፣ ሕገ አራዊትን ከዳሰስን በኋላ ሕገ ልቡናን እንቃኛለን።

## ፩ኛ ሕገ አራዊት፦

የሕገ አራዊት መመሪያ ነፍስ መግደል ውሸት እያፈለቁ መናገር። በእውነት አለመቆም፣ እውነትን መሸሽ፣ መደበቅ፣ መሰወር እና ራስን መውደድ ናቸው። እነዚህም ጠባያተ ፍጥረት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰይጣን እንደሆኑ ከዚህ በታች እንዲህ እያለ ገለጻቸው።

፩ኛ፦ "ውእቱሰ ቀታሌ ነፍሰ ሰብእ"

፪ኛ፦ "ውእቱ እምትካቱ ኢይቀውም በጽድቅ እስመ አልቦ ጽድቅ በሀቤሁ"

፫ኛ፦ "ወሶበሂ ይነብብ ሐሰተ እምዚአሁ ይነብብ እስመ ሀሳዊ ውእቱ ወአቡሃ ለሀሰት"

እያለ ደጋግሞ ከገለጸ በኋላ የህገ አራዊት ተከታዮችን ባህርያት እንደሚከተለው ገልጿቸዋል።

፩ኛ "አንትሙሰ እም አቡክሙ ሰይጣን አንትሙ ወፍትወቶ ለአቡክሙ ትገብሩ።

፪ኛ "አንትሙሂ ዘርኢክሙ በሀበ አቡክሙ ትገብሩ"((ዮሐ ፰፥፴፰—፵፬)

፫ኛ "ወዐሳብሰ ይኅይይ እስመ ዐሳብ ውእቱ ወኢየሀዝኖ በእንተ አብግዕ"

እያለ ገለጻቸው።

ህገ አራዊት በመጀመሪያው ሰው በአዳም ቤት በአቤል እና በቃኤል ህይወት ተከሰቱ። ቃዔል በህገ አራዊት ተገፋቶ ወንድሙን አቤልን አጠፋ። ራሱንም በህገ አራዊት ለመምራት ወደጫካ ገባ። ከዚያች ቅጽበት ጀምሮ ዓለም የነብር እና የዓንበሳ ከተማ ሆነች። ጉልበት የሌለው ጉልበት ላለው ምግብ ሆነ። የሰው ኑሮ በህገ አራዊት በአንበሳና በሚዳቋ፣ በነብርና በበግ ግልገል፣ በበይና በተበይ ግንኙነት መካከል ላይ ተመሰረተ። ሰው በበይና በተበይ ግንኙነት መኖር ጀመረ። ህገ አራዊት የሆነው የሰይጣን ባህያት የሚጋልባቸው ቃኤልን የመሳሰሉ ሰዎች ዓለምን ተቆጣጠሩ።

ይህ በቃኤል ላይ የታየው ሕገ አራዊት ሳይዳስሰው ያለፈ ትውልድና ዘመን የለም። ዘመኑን እና ትውልዱን የከፋ የሚያደርገው ግን በሕገ አራዊት የሚመሩ ሕገ አራዊትን በምሳሌነት በትውልድ ጭንቅላት ላይ የሚቀርጹ ሰዎች በዝተው መሪነቱንና ምሳሌነቱን ሲይዙ ነው። ያገኙትን ሁሉ ሰውም እንስሳም መሬት ሳይቀር እየጋጡ መብላት አልበቃቸው ብሎ "ለእመ ሀልቀ ሰብእ ሠዑ ሰብአ" ማለትም "የምትሰዋው ላም ካጣህ ሰውን ሰዋ የሚል፣ ሰው—በላ አምላክ ፈጠሩ።

ህገ አራዊትን ተክታ ሚዛናው ፍርድ ይዛ ብቅ ባለችው በህገ ኦሪት ዘመን እንኳ የሕገ ኦሪት አስተማሪዎች እና አስከባሪዎች ነን የሚሉትን ሰዎች ህገ አራዊት እንደተቆጣጠራቸው "ትቀትሉ፤ ትሰቅሉ፤ ትቀስፉ፤ ትሰድዱ እምሀገር ውስተ ሀገር ከመ ይብጻህ ላዕሌክሙ ደመ ኩሎሙ ጻድቃን ዘተክዕዎ ዲበ ምድር እምደመ አቤል ጻድቅ እስከ ደመ ዘካርያስ ወልደ በራክዩ ዘተክዎ በቤተ መቅደስ ትውልደ አራዊተ ምድር በእፎ ትክሉ አምስጦ እምኲነኔ ገሀነም (ማቴ ፳፫፥፩ —፴፭)" እያለ ክርስቶስ መሰከረባቸው።

# ሕገ ልቡና ወይም ንጽሐ ጠባይ (concious)

በሕገ አራዊት የሚመራውን ህዝብ ታዝበው የራሳቸውን ህሊና ጠብቀው በመታገል በንጹህ ሕሊና ህይወታቸውን የፈጸሙ በጣም ጥቂት ሰዎች ነበሩ። ይሁን እንጅ ከዚህ በታች እንደምንመለከታቸው እነሱም ቢሆኑ ከህገ አራዊት ንክኪ አላመለጡም።

ለምሳሌ፦ "ወሰትየ ወሰክረ ወተአርቀ በውስተ ቤቱ" እንዲል ኖኅ ጠጥቶ ሰከረ። ሰክሮም በልጆቹ ፊት ራቁቱን ወደቀ። "ወምድርሰ ሀለወት እምትካት ዕራቃ" ህይወት አልባ እንደነበረችው መሬት ራቁቱን ሆነ። "ወይቤ ኖኅ ርጉመ ይኩን ከነአን ወገብረ ወነባሬ ይኩን ለአኀዊሁ"( ዘፍ ፱፥ ፳፪_፳፭) ከዚያ በኋላ በልጆቹ መካከል የገዥና የተገዥ መንፈስን አመነጨ። ይህ በኖህ ላይ የተከሰተው ህገ አራዊት እንጅ ህገ ልቡና ወይም ንጽህ ጠባይ የሚባል አይደለም።

አብርሃምም "አማን እኅትየ ይእቲ እመንገለ አቡየ ወአኮ እምንገለ እምየ። ወኮነተኒ ብእሲትየ" (ዘፍ ፳፥፲፪) እህትነቷ ባባቴ ጎን በመሆኗ አገባኋት በማለቱ፤ በዘመኑ በሴት በኩል የሚዛመዱ ማግባት ክልክል እንደነበር ቢያሳይም፤ እውነቱን ለመናገር ግን እስኪጠየቅ መዘግየት አልነበረበትም። ባካባቢው የነበረው ህዝብም "አልቦ ፍርሀተ እግዚ ውስተ ዝ መካን፡ ይቀትሉኒ በእንተ ብእሲትየ" ማለትም "በስፍራው የሚኖረው ህዝብ በህገ አራዊት የሚመራ እንደሆነም ጠቁሟል። "፲፩)

የታወቀው የክርስትና መምህር የሆነው ቅዱስ ጳውሎስም ሁለቱም ህገ አራዊትና ህገ ልቡና በሰዎች መካከል እንዳሉ "ወያርእይዎ ገቢረ ሕግ እንዘ ጽሑፍ ውእቱ ውስተ ልቦሙ ።ወያርሰሐስሐሙ ልቦሙ ወይቀልዮሙ" (ሮሜ ፪፥፲) በማለት በህገ አራዊትና በህገ ልቡና መካከል ያለውን ትንቅንቅ ጠቆመ። እንዲያውም "አንሰ ሎቱ እትቀነይ በሥጋየ በልብየኒ ወበ ህሊናየ ለሕገ እግዚአብሔር ወበነፍስትየኒ ለሕገ ኃጢአት (ሮሜ ፯፥፳፭) እያለ ሁለቱ የጦር ሜዳቸው አደረጉኝ ህገ አራዊት አሸንፎ ልቤን መንፈሴን ማርከው። እያለ በራሱ ህሊና ላይ ይካሄድ የነበረውን ተማሮ ተናገረ።

"ተጻብአ ወተቃተለ ምስለ ዝኩ ሕገ እግዚ ዘውስተ ልብየ ወሀየለ ዝኩ ሕገ ኃጢአት ዘውስተ አባልየ ወጼወወኒ መንገሌሁ(፯፥ ፳፫) በማለት የተሰማውን ተናገረ።ሰ "ወአንሰ በሥጋ ወደም ሥዩጥ ለኃጢአት (ሮሜ፯፥፲፬) እየለ ተናዘዘ። ለምናደርጋት ነገር ሁሉ ህሊናችን ተከፍሎ ይሟገታል። ህሊናችን ይፈርዳል። እየፈረደብን እናደርገዋለን። ነገር ግን የህሊናችን ትክክለኛ ፍርድ ብንከተል በእግአብሄር ፊት ነጻ ነን አለ። "ወንህነሰ "ቅድሜሁ ናመክሮ ልብነ። ወእመሰ ያርስሀስሀነ ልብነ እምአበሳነ ወየዐብዮ… እመሰ ኢቀልየነ ልብነ ገጽ ብነ በሀበ እግዚአብሔር"(፩ኛ ዮሐ ፫፥፲፱—፳፩)

ሕገ ልቡና (ንጽሐ ጠባይ) ምንጩ እግዚአብሔር ነው። "ወአንሰ ዘርኢኩ በኀበ አቡየ እነግር" "ወእመሂ ኮንኩ አነ ጽድቀ እኄንን እስመ ኢኮንኩ ባህቲትየ አላ ወአብ ዘፈነወኒ" (ዮሐ ፰፥፲፮) "ወዘልፈኒ ሀሎ ምስሌየ ወኢይሀድገኒ አብ ባህቲትየ እስመ አነ እገብር ስምረቶ ዘልፈ" እያለ እንደተናገረው ከክርስቶስ የተሰማው ሲያደርግ የታየው የፈለቀው ከእግዚአብሄር ነው። እኔ ቅዱስ እንደሆንኩ እናንተም ቅዱሳን ሁኑ እያለ መመሪያ (Prolongation of reference) ሰጠ ።

ሕገ አራዊትም ህገ ልቡናም በጽሁፍ የማይወረሱ ናቸው። እንደ ኦሪት ሕግ በድንጋይ ወይም በብራና የተጻፉ አይደሉም። በሰው ህሊና የነበሩ ናቸው። ከላይ እንዳልኩት ከሕገ አራዊት ጋራ በመታገል እየወደቁ እየተነሱ ህይወታቸውን የጨረሱ "የውሀቱ ለአቤል ዘተቀትለ በአመጻ፤ ሂሩቱ ለሴት፤ ወምግባቲሁ ለሄኖክ" እየተባሉ ። ጥቂት ፳ ሰዎች እና ነብያት በአባ ህርያቆስ መጽሀፈ ቀዳሴ የተደረደሩት ተጠቅሰዋል።

እንደነ የኔታ ፍስሀ ከነበሩት ምርጥ ሊቃውንት እንደሰማሁት፤ አዳም ሲረገም ያመለጠች ነጭ እንቁ የደም ጠብታ ከትውልድ ወደ ትውልድ እየዘለለች መጥታ ከሀና ማህጸን ላይ ስትደርስ ማሪያም ሆነች እያሉ እመቤታችን ከአዳም ሰውነት ለይተው ለመቁረጥ የሚሞክሩትን የአላዋቂዎችን ፈጠራ፤ እጅግ ይጸየፈዋል። "ኮነኖሙ ዳእሙ ሞት እምአዳም እስከ ሙሴ ለእለሂ አበሱ ወለእለሂ ኢአበሱ እስመ ኩሉ በአምሳለ አዳም ተፈጥረ" (ሮሜ ፭፥፲፬) ብሎ ቅዱስ ጳውሎስ የተናገረውንም መሰረት በማድረግ እነ የኔታ ፍስሀ የሰሞነኞችን ተረትና ፈጠራ ይቃወሙታል።

በተለይ"እምአዳም እስከ ሙሴ" የምትለዋ ሀረግ "የገደለ ይገደል ያቆሰለ ይቁሰል" የምትለው ሕገ ኦሪት ብቅ ከማለቷ በፊት የነበረውን ሕገ አራዊት የምታሳይ ቀስት እንደሆነች እነ የኔታ ፍስሐን

የመሳሰሉ አባቶች ይናገራሉ። ያም ሆነ ይህ፤ ህገ ልቡና በጥቂት ሰዎች ብትኖርም; በሕገ አራዊት ተጽእኖና ቁጥጥር ስር ነበረች ይላሉ።

# ፪ኛ ሕገ ኦሪት፦

"ኢትግበሩ ዓመጸ በውስተ ፍትሕ ወኢታድልው ለገጸ ነዳይ ወኢታድልዑ ለገጸ ዓቢይ በጽድቅ ኮንኖ ለከልእከ" (ዘሌ ፲፱፡፲፭) ፍርድ አታዛቡ። ድህም ከዋሸ ድሀ ነው ብላችሁ አትፍረዱለት። ንብረት ያለውም ንብረት ስላለው ከዋሸ ፍረዱበት። ፍርድ ሚዛን ናት። "ቅድመ ዘሲበት ተንሥእ ወአክብር ገጸ አረጋዊ"(ዘሌ ፲፱፡፴፪) ታሪክ መስካሪ ድንበር አደራዳሪ ነውና ሽማግሌውን አክብሩ ስሙ" "የገደለ ይሙት። ዓይን ያጠፋ ዓይኑ ይጥፋ። ጥርስ የሰበረ ጥርሱ ይሰበር" የሚለውን ሚዛናዊ (ርቱዕ ፍትህ) ተብሎ የተጻፈበትን ጽላት ይዛ የነብር እና የዓንበሳ ከተማ ወደ ሆነችው ዓለም ብቅ አለች።

ይህም ማለት አንድሰው ጉልበት አለኝ ብሎ የሰው ዓይን ከማጥፋቱ በፊት በራሱ ዓይን መጥፋት ላይ መፍረድ አለበት። ቢገድል መሞት እንዳለበት በራሱ መፍረድ አለበት። ይህች በጽላቱ ላይ የተጻፈች አስቀድሞ በራስ የመፍረድ ፍትህ፤ ከህገ አራዊት ማለትም ካንበሳና ከተኩላ ስርአት የተለየች ሚዛናዊት "ርቱዕ ይደሉ" የተባለችው ሕግ ናት።

## ሀ. ፲ቱ ቃላት የተጻፈበት ጽላት

በዘመነ ኦሪት የሚመለከው አምላክ ዛሬም የምናመልከው ነው። አምልኮቱ ለሚከናወነው ስርአት ማእከል "ፍትህ ርትዕ" (ሚዛናዊ ፍርድ) የተጻበት ጽላት ነበረች። ከርስቶስ የሁሉ ፍጻሜ ነውና "ህግን ልፈጽም እንጅ ልሽር አልመጣሁም" እንዳለው፤ ሁሉንም ጠቅልሎ ለመፈጸም ራሱን መስዋዕት አድርጎ በማቅረቡ "ለእመ ሀልቀ ላህም ሱዑ ሰብእ" የሚለውን ህገ አራዊትንም ፈጽሚል። ሕገ ኦሪት ቢፈጸምም በስሙ መስዋዕት ሲከናወንበት የነበረችው፤ ፈቃዱንና ሃይሉን የገለጸባትን ጽላት ሥጋ የሆነው ቃል ያወጀው ጽድቅ የነግሦቢታል። ተቀበሉት ብሎ የሰጠነን ሥጋውንና ደሙን በዚህ ጽላት ላይ አንግሰን እናቀርበዋለን። ይህችንም ጽላት እንደጥምቀት በመሳሰሉ በዓላትና በውጭና በውስጥ በሚነሱት የሰውን ህይወት የሚያደፈርስ ህገ አራዊት በተከሰተበት ቦታና ጊዜ ሁሉ፤ የጽድቅ በሯ በመጥበቡ ከጽድቅ መድረስ ቢያቅታችሁም ከህገ አራዊት ውጡ! ወደ ፍትህ ርትእ ለመመለስ ጣሩ! ለማለት ቤተ ክርስቲያናችን ጽላቱን ይዛ ብቅ ትላለች።

## ለ. ይህ ጽላት አሁን ለምን አስፈለገ?

ጥምቀት የመነጨው በዘመነ ሐዲስ በክርስቶስ ነው። ጽላት የነበረው ማዕከላዊነት በዘመነ ኦሪት ነው። ታዲያ ሁለቱን ጥምቀትንና ጽላትን ምን አገናኛቸው? እኛስ ከዓለም በተለየ መንገድ ለምን ሁለቱንም አዋህደን በጥምቀቱ በዓል እናጸባርቃቸዋለን? የሚሉ ጥያቄዎች ሊነሱ ይችላሉ እና መመለስ ያለባቸው ይመስለኛል።

በእምነቱ ያለውን የትርጓሜ ተዋርሶ ልተወውና ህዝባዊ ወደ ሆነው ሀሳብ በመሻገር ባጭሩ እንመልከተው።

"አሮን ነደቀ ምሥዋዐ አንጻሮ ወአያደ እንዘ ይብል በዓለ እግዚእ ጌሰም"(ዘጸ ፴፪፡፭) አሮንና ህዝቡ ከህገ አራዊት (እንስሳ) ባለመላቀቃቸው በእንስሳ ምስል እግዚአብሔር ያልፈቀደውን ለህዝብ የማይጠቅም ባዶ በአል ለማድረግ ሰከሩና፤ "ይበልኡ ወይሰትዩ ወተንሥኡ ይዝፍኑ ወይትዋነዩ(፴፪፡፮) በጽላቱ ላይ ከተጻፈው ፍትህ ርትእ ጋራ ተስማሚ ባልሆነ፤ ነገር ግን በሕገ አራዊት እየተገፉ ሥጋቸው የፈቀደውን እያደረጉ ጽላቱን ሊቀበሉ ሞከሩ። ጽላቱ ከሕገ አራዊት ጋራ አንድነት ስላልነበረው ከነሱ ጋራ አልዘለቀም።

"ወሶበ ቀርበ ሙሴ ኀበ ትእይንት ርእዮ ለውእቱ ላህም ወተውኔት ወተምአ ወገደፎን እምውስተ እደዊሁ ክልኤ ጽላተ ወቀጥቀጦን በታህተ ደብር። ሙሴ የአሮ ንና የህዝቡን ህገ አራዊታዊ ባህርይ ባየ ጊዜ ትእግስቱ አለቀ። ተቆጣ ጽላቱን ለቀቀው ሰበረው። "ወነስአ ለውእቱ ላህም ዘገብሩ ወአውአዮ በእሳት ወሀረጾ ወዘረዎ ውስተ ማይ ወአስተዮሙ ለደቂቀ እስራኤል።((ዘጸ ፴፪፡፳) ጣኦት የተሰራበትን ስብርባሪ በውሀ በጥብጦ ስራልን ብለው አሮንን ያስገደዱትን ሰወች አጠጣቸው። ዲዮቅልጥያኖስ የሚወደውን ወርቅ አቅልጦ አባ አጋግዮስ የተባለውን መነኩሴ የጋተው ይህን ምሳሌ በማድረግ እንደሆነ ሊቃውንት ይናገራሉ። ሙሉ ታሪኩን ለማንበብ ከፈለጉ http://medhanialemeotcks.org ብለው ይፈልጉ ወይም በጉጉል አባ አጋግዮስ ብለው ይፈልጉ።

ሙሴ  ሕገ አራዊት ባስከተለው ጥፋት እጅግ አዘነ። “ሙሴ ለአሮን ምንተ ረሰየከ ዘንተ ህዝበ ከመ ታምጽእ ላዕሌሆሙ ኃጢአተ ዓቢየ”፳፩ ማለትም፡- ምነው አሮን ? በዚህ ህዝብ ላይ መከራ ለማምጣት ይህን ለምን አደረክ? ብሎ በአሮን ላይ እጅግ አዘነ። አሮንም “ወይቤሎ  አሮን ለሙሴ ኢትትመዓዕ ላእሌየ ለሊከ ተአምር ግእዞሙ ለእሉ ህዝብ።፳፪ ማለትም፡- የዚህን ህዝብ ጠባይ አንተ ታውቅ የለም? ለምን በኔ ትፈርዳለህ? ብሎ በህዝቡ አመሀይኝቶ ከወቀሳው ሊያመልጥ ሞከረ። በዚህ ምክንያት በበርሀ ወድቆ ቀረ።

“ክርስቶስ የተጠሩ ብዙወች የተመረጡ ጥቂቶች ናቸው” እንዳለው ሰው ከጽድቅ መድረስ ይቅርና  ከሚዛናዊቷ ፍትህ መድረስ አልቻለም። በሕገ አራዊት እየተመሩ የሰው አገር ይወሩ የነበሩት የተጠመቁ ናቸው። በክርስትና ስም አገር ይወሩ ለነበሩት እንኳን በጥምቀት ክርስቶስ ካወጃት ጽድቅ ልትደርሱ ከሚዛናዊቷ ፍትህ ገና አለደረሳችሁም ለማለት ጽድቅ የነገሰችበትን ጽላት ከፍ አርጎ ማሳየት አስፈላጊ ሆነ።

በሕገ አራዊት ተሰቃየን ፍትህ ርትእ ተጠማን እያለ ለሚጮኸው ደቂቀ ዓዳም ከሚዛናዊ ፍርድ ከሕገ ኦሪት እጅግ የተሻለ እጅግ የራቀ፤ የረቀቀ እና የጠለቀ ለዚህ ዓለም የሚጠቅም፤ ወደ ሚመጣውም ዓለም የሚሻገር “ለቀደሙት አትግደል የተባለውን ሰምታችኋል በወንድሙ ላይ የሚቆጣ ሁሉ ፍርድ ይገባዋል” ((ማቴ ፭፡ ፳፩) በማለት የምታውጀውን ጽድቅ የተባለችውን መርሆ ክርስቶስ እያወጀ መጣ።

# ፫ኛ፡- ሕገ ክርስቶስ (ጽድቅ)፡-

በንጽሀ ልቡና እየተደገፉ በኦሪት ውስጥ የነበሩ አብርሃምን የመሳሰሉ ሰዎች “አብርሃም አቡክሙ ተመነየ ከመ ይርአይ ዕለትየ ርእየሂ ወተፈስሀ”(ዮሐ ፰፡፶፮) እንዳለው በክርስቶስ የምትታወጀውን ጽድቅን አሻግረው በማየት በተስፋ ተመኟት። የቀሩት ነብያትም “እግዚአብሄር አየ ፍርድም እንደሌለ ተከፋ ሰውም እንደሌለ አየ። ተደነቀ። ስለዚህ የገዛ ክንዱን መድኃኒት አመጣለት ጽድቅም አገዘው። ጽድቅንም እንደ ጥሩር ለበሰ (ኢሳ ፶፱፡፲፯) እያሉ ተነበዩላት።

ክርስቶስም “ብዙዎች ነብያትና ጻድቃን የምታቱትን ሊያዩ  ተመኝተው አላዩም፤ የምትሰሙትን ሊሰሙ ተመኝተው አልሰሙም፤እናንተ በማያታችሁና በመስማታችሁ ብጹአን ናችሁ(ማቴ ፲፫፡፲፯) እያለ ይህችን ጽድቅ አይተውና ሰምተው ለምስክርነት ላዛጋጃቸው ክርስቲያኖች ተናገረ።

ኦርቶዶክሳውያን ሊቃውንት እነ ቅዱስ ባስልዮስ ይህች ጽድቅ እንዴትና በምን ሁኔታ እንደ አወጃት “እስመ ክርስቶስ ፍጡር ውኢፍጡር ውእቱ። ኀብሩ በ፩ዱ ህላዌ ወአካል ኀቡረ ንብል ኢፍጡር እስመ ውእቱ ቀዳማዊ እምቅድመ ዓለም ወእስከ ለዓለም። ወውእቱ ፈጣሬ ኩሉ ዘህሎ  ወዘሰ ንቤ ፍጡር በእንተ ዘተሳተፈ ሥጋ ድካመነ በሥርአት ዘገብሮ በእንቲአነ . … ( ፴፭፡ ፪—፲፪)  እያሉ አረጋግጠው መሰከሩ።

በጽላቱ ላይ በተጻፉት ፲ቱ ቃላት የሚመሩ ሰዎች፤ በዘመነ አራዊት ውስጥ ለነበሩ ሰዎች ከህገ አራዊት ህጋቸው እንዲወጡ፤ በህገ ኦሪት የነበሩ ሰዎች ደግሞ ወደ ህገ ክርስቶስ ማለትም ወደ ጽድቅ እንዲሻገሩ ምሳሌ እንዲሆኗቸው በየደረሱበት ለትውልዳቸው ምሳሌዎች እንዲሆኑ ተዘጋጁ። በክርስቶስ ሕግ (ጽድቅ) ያሉ ሰዎች ደግሞ በዘመነ ኦሪት ለነበሩ ሰዎች ምሳሌ ይሆኑ ዘንድ የበቁ እንዲሆኑ ተነገራቸው።

ሕገ ኦሪትን ተቀብለናል ያሉ ሰዎች ይሁዲም ይሁኑ ሙስሊም፤ ከህገ አራዊትነት ተላቀናል፤ ኦሪት በምታወጀው ፍትህ ርትእ ከምትባለው እርከን ላይ ደርሰናል፤ ብለው ነው። በክርስቶስ አምነን ተጠምቀናል የምንል ደግሞ ከኦሪቱ ሚዛናዊ ፍርድ ላይ የነበርንበት እድገት ጨርሰን በጥምቀቱ ካወጀት ጽድቅ እርከን ላይ ደርሰናል ብለን ነው።

# ሀ. ጽድቅ ምንድን ናት?

“ጽድቅ ክርስቶስ መንግስቱን የሚመራበት መርሆ ናት” (ኤር ፳፫፡ ፭)። ጽድቅ በነቢዩ ኢሳይያስ ንግግር እንደተገለጸው (ኢሳ ፶፱፡፲፯—፲፯) በሕገ ኦሪት የታወጀችው ሚዛናውቷ ፍርድ እድገቷን ስትጨርስ የመጣች መርሆ ናት። በነቢዩ ኤርምያስ እንደተገለጠው ጽድቅ የክርስቶስ ሌላ መጠሪያ ስሙ ነናት ( ኤር ፳፫፡፮)።የዲያብሎስን ሽንገላ (ህገ አራዊትን) መቃወሚያ መሳሪያ ናት (ኤፌ ፮፡ ፲፩። ጽድቅ የህገ አራዊት መንፈስ በጭንቅላታችን እንዳይገባ መከላከያ ጥሩር ናት (ኤፌ ፮፡ ፲፬። ጽድቅ በህገ አራዊት ከመጥፋት ለመዳን ራስ ቁር ናት።ጽድቅ ራስን አስክዳ ለህዝብ ለወገን መቆም የምታስችል መሳሪያ ናት። “ኢየሀስስ ተድላ ለርእስየ”(ዮሐ ፳፡፶)። “ከመ ይጼወው ኩሉ ልብ ወሕሊና ወይግነይ ለክርስቶስ ( ፪ ቆር ፲፡፭) እንዳለው ክርስቶስ፤ በህገ አራዊት ያሉትን ከህገ ኦሪት እርከን ላይ፤ በህገ ኦሪት ያሉትን ደግሞ ከጽድቅ እርከን ላይ ለማድረስ መማሪያኪያ መሳሪያ ነው።

ክርስትናን ከሁሉም እምነቶች ልዩ ከሚያደርጉት አንዱ፤ ክርስቶስ ሲጠመቅ ያወጃት ጽድቅ ናት። ይህም ማለት አንድ ሰው እጽፍ ድርብ ዋጋ የሚያስጠይቅ በደል ቢፈጸምበት፤ተበዳዩ ለተፈጸመበት ተመጣጣኝ ዋጋ መጠየቁን ትቶ፤ የበደለውን ይቅር ብሎ የበደለውን መውደድን ነው። ለዚህም ማስረጃነት ክርስቶስ ራሱ ተሰቅሎ ራሱን የሰቀሉትን ሰዎች የሚያደርጉትንም አያውቁምና ይቅር በላቸው ብሎ እራሱ ከክርስቶስ ከተናገረው የበለጠ ገላጭ ምሳሌ አይገኝም ብለው ሊቃውንቱ ይደመድማሉ።

ሆኖም በቅዱሳት መጻህፍት ቅኔወቻቸውን ያበለጸጉ የቅኔ መምህሮቻችን፤ እኛ ተማሪዎቻቸው እንደነሱ ቅኔያችንን ከተራነት አውጥተን ከፍ ለማድረግ ይረዳ ዘንድ የታሪክ መጻህፍትን ባንድምታ እንድንማራቸው ያስገድዱናል። ቅኔያችንን ከምናበስልባቸው ከብዙዎቹ ቁም ነገሮች አንዱ በመጽሐፈ ነገስት ካልዕ በ፯ኛ ምዕራፍ የተጠቀሱት ምሳርና የእንጨት ቅርፍት ማሳሌ ነው። በውሀው ውስጥ የሰመጠውን ብረት ለማንሳፈፍ ቅርፍቱ ብረቱ ወደሰመጠበት ጥልቀት ውስጥ ሰመጠ። ቅርፍቱ የብረቱን ክብደት ተሸክሞ በመስጠም፤ የራሱን መንሳፈፈ ለብረቱ በመስጠት ብረቱን አንሳፈፈው። በዚህ ላይ የተዘረፈውን ቅኔ ተቀብያለሁ። እራሴም ቆጥሬበታለሁ። ጽድቅ ማለት ይህ ነው።

አትናቴዎስ የተባለው የመጀመሪያውን ጳጳስ ወደ ኢትዮጵያ የላከው ሊቅ “ክርስቶስ ቦአ ውስተ መርገም በእንቲአነ እንዘ ኢይቀርቦ መርገም፡አላ ሰምረ ከመ ይጹር መርገመ ዚአነ ወበእንተ ዝንቱ ተብህለ ከመ ውእቱ ቦአ ውስተ መርገም(፴፡፬) እያለ ገለጸው።

ክርስቶስ የአዳምን ዘር ከሰመጠበት ጉድጓድ ህገ አራዊትና ከዚያም በላይ በጥፋት በመካካስ መጠፋፋትን ከምታውጀው ሚዛናዊ ፍትህ ከተባለችው ሕገ ኦሪት ያላቀቀን ዘንድ እንደኛ ሰው ሆኖ ጽድቅን አወጀለን። “ይእዜሰ እንተ ትሄይስ መልእክተ አድምአ ወለእንተ ተዐቢ ሥርየተ ኀሩየ፡ ኮነ ወሠርአ ተስፋ እንተ ትኄይስ (ዕብ ፳፡፮)።”ማለትም፦ በክርስቶስ የታወጀችው ህግ ከቀደሙት ህግጋት ከህገ አራዊትና ከህገ ኦሪት የተሻለች ከዚህ ዓለም ዘልቃ የምትሄድ ህግ ናት።

ክርስቶስ ጽድቅን እንዴት እንዳወጀ ለማወቅ የምትፈልጉ የዚህን ሰንሰለት ማግኝት መቻላችሁን በመጠቆም ወደ ስርአቱ እሻገራለሁ።

# ለ. የጥምቀት የአከባበር ስርዓት

ጽድቅ ክርስትና ካወጀት ጽድቅ ጎደለ ብሎ ሳይሆን ጽላቱ ስለተሸከመው ፍትህ ርትዕ ጎደለ በህገ አራዊት በጨለማ ተሰቃየን እያለ ገና በመጮህ ላይ ነው። ፍትህ ርትዕ አጎደሉ ተብለው በመከሰስ ላይ የነበሩት ተጠምቀናል የሚሉ ሰዎች ናቸው። እነሱን ለማሳፈር እንኳን ከጽድቅ ልትደርሱ ገና ከአራዊት ህግ አልተላቀቃችሁም የሚለውን መልእክት ለማስተላለፍ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ጽላት ተሸክማ ወደ ወንዝ የምትሄደው ማታ ነው።

ማታ፡- የሚወጣበት ምክንያት ኦሪት ፍትህ ርትእን ብታውጅም የዓለም ሰዎች ከህገ አራዊት ከጨለማው ስርአት አለመውጣቱን ለማሳየት ነው። ጽላቱን ተሸክመውና አጅበው የሚወጡት ታዳሚው ብዙ ሲሆን የገባው ጥቂትነቱን ለማሳየት ነው።

ውሀ፡- "ወመንፈሰ እግዚአብሔር ይጼልል መልዕልተ ማይ" በትርጉሙ ትውልድ ይድረስበት ይሉና ውሀና መንፈስ የተሳሰሩ ናቸው። ውሀ የህወት ምንጭ ነው። በጥምቀትም የሚፈጸመው ጽድቅ እንደገና መወለድ ሲሆን የሚከናወነው 1በውሀና በመነፈስ እንደሆነ ተነግሯል። ትውልድ እንደው ውሀ ፈሳሽ ጎርፍ ነው። በሰርጎ ገብ ጭቃም ደፍራሽ ነው ይላሉ ። በመንፈስና በውህ መካከል ያለውን ምሥጢር "ድህረ ይመጽኡ ይበይኑ" ብለው ያልፉታል። ይህ አባባላቸውንም የዘመናችን የስነ ተፈጥሮ ሊቃውንት ውሀን የህወት ሰጭ ፍንጭ አድርገው በመጠቀማቸው ተርጉመውታል።

በሽብሸባው በቅኔው በእልልታው የሚካሄዱትን ለመግለጽ የዚህች ጦማር አቅም ስለሚገታ በጣም አስደናቂ የሆነችውን በጎልማሶች ብቻ የምትንጸባረቀውን ሆታ ብቻ እንመልከት።

# ሐ. ጎልማሶች "ኦ ሆ!" የሚሏት ከምን ፈለቀች?

"ኦ ሆ" የምትለው ቃል፤ ቃለ አጋኖ እና ቃለ አህስሮ ትባላላች። ማለትም ተደናቂ የሆነውን ሰውም ሆነ አስደናቂውን ነገር አክብሮና አጋኖ ለመቀበል። አጸያፊና አስቀያሚ ነገር የሰራውን ሰራውንና የተሰራውን ነገር አቃሎ አዋርዶና ተጸይፎ ለመጣል የምታስችል የስሜት ገላጭ ቃል ናት።

በጥምቀት በአል በጽላቱ ዙሪ የሚደረገው ሆታ ቢቻል ጽድቅን፤ ባይቻል ደግሞ ሚዛናዊ ፍርድ የምትሰብከውን ሕገ ኦሪትን መቀበልን ያንጸባርቃል። "ለእመ ሀልቀ ላህም ሱዑ ሰብአ" ማለትም፤ የምታርደው እንስሳ ካጣህ ሰው እረድ" የምትለውን ህገ አራዊትን ንቆ አቃሎ አዋርዶ የመጣልን መልእክት ይወነጭፋል። ይህን ያስተማሩ በጥምቀቱ ያወጀትን ጽድቅን እንዲያስተምሩ ክርስቶስ ሑሩ ብሎ ወደ ዓለም የላካቸው ሐዋርያት ናቸው።

፩ኛ፡- ቅዱስ ጳውሎስ "ኦ ሐ! ትብልዋ ወኀበርክሙ ተአብሱ አግብርቲሁ አንትሙ ትከውኑ ለሞት"(ሮሜ ፮፡፲፮) በህገ አራዊት መርኋቸው እየተመሩ በደል ከሚፈጽሙ ጋራ ብትተባበሩ በነፍስ በሥጋ የታሪክ የሞራል ሙታኖች ናችሁ። ስለዚህ "ኦ ሐ! ብላችሁ በመነሳት ተቃወሚቸው እንጅ አትተባበሯቸው" እያለ ሰበከ።

፪ኛ ራሱ ቅዱስ ጳውሎስ "ወእመሰ ለጽድቅ ኦሐ! ትብልዋ ወኀበርክሙ ውስተ ሠናይ አግብርተ እግዚአ አንትሙ (፮፡፲፮) ክርስቶስ ባወጀት ጽድቅ በመተባበር ኦሐ! ብላችሁ ተባብራችሁ ብትነሱ የጽድቅ ሠራዊት ትሆናላችሁ። እያለ ደገመው።

፫ኛ ቅዱስ ያዕቆብም "ኦ ሆ በልዎ ለእግዚ ወእንብየ በልዎ ለጋኔን ወይጎይይ እምኔክሙ (ያዕቆብ ፬፡፯) ስለዚህ የጽድቅ ተቃራኒ የሆነውን ጋኔንን እምቢ በሉት። እያለ በሙሉ ልብ ተናረገው።

ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት "በሕገ አራዊት የሚጫናችሁን ቀንበር እምቢ ብላችሁ ስበሩት፤ ቀንበሩን ሊጭንባችሁ የሚሞክረውንም አሳፍሩት" ብለው የሰሩላቸውን ስነ ልቡና፤ ጽድቅ በታወጀችበት በጥምቀቱ በዓል ላይ ኢትዮጵያውያን ጎልማሶች ያካሄዱት የነበረውን እንቅስቃሴ የተመለከቱ የውጭ ጸሀፊዎች የሚከተለውን ምስክርነት ሰጥተዋል።

# መ. የታሪክ ምስክርነት

የኢትዮጵያውያንን ኀልማሶች ሆ ታ ትርጉምና መሰረታዊ አመጣጥ ከሀዋርያት ትምህርት እንደተወሰደ ከብቸናው የቅኔና የመጽሐፍ ትርጓሜ ሊቅ ከነበሩት የኔታ ፈረደ ከዚያም የመጻህፍት ምስጢር ምንጭ ከነበሩት ከደብረ ሊባኖሱ የኔታ ፍስሀ ብሰማውም፤ እጭንቅላቴ ላይ የደወለው እንግሊዞች በቅዱስ እንድርያስ ስም ኬንያ በከፈቱት ኮሌጅ በቆየሁበት ወቅት የኛን ታሪክ ካጠኑት ከእንግሊዛዊው Dr. Smith እና ኬንያዊው Bishop David Gitaree በሰማሁበት ቀን ነው።

Dr. Smith ወራሪወችን Bishop David Gitaree ደግሞ ተወራሪወችን ከሚወክሉ ሊቃውንት ስለ ኢትትዮጵያ ሲናገሩ ከመስማት ለኔ ቢጤ ለቆሎ ተማሪ የበለጠ መታደል ያለ አይመስለኝም። ሁለቱም ከዚህ የሚከተለውን ተናገሩ።

“ኢትዮጵያውያን የጥምቀትን እና የደመራን በዓላት ሲያከብሩ በጽላቱ ዙሪያ ሴቱ ለጥምቀት ያልሆነ ቀሚስ ይበጣጠስ እያለ በእልልታ፤ ኀልማሰው በሆታ፤ የሚያደርገውን እንቅስቃሴ፤ ኢትዮጵያን ያአጎራብቱ አገሮችን ቅኝ በመግዛት ላይ የነበሩ ምዕራባውያን ባለስልጣናት፤ድንበር እየተሻገሩ ወደ ኢትዮጵያ በመግባት ይመለከቱ ነበር። ቅኝ ገዥዎች ድንበር ተሻግረው ሲመጡ ይገዟቸው ከነበረው ህብረተ ሰብ ከህንድ ከግብጽ፤ከኬንያና ከቀሩት ሁሉ ቅኝ ግዛቶቻቸው እየመለመሉ የወታደር ማእረግ በመስጠት በስራቸው ባዘጋጁቸው ተገዥዎች ታጅበው በበዓሉ ላይ የሚካሄደውን ለመመልከት ወደ ኢትዮጵያ ይሻገሩ ነበር። በበዓሉ ዙሪያ በካህናቱ የሚሸበሸውን፤ ኀልማሶች የሚያስተጋቡትን አ ሆ ታ፤ ሴቱ ወንዱ ያሚያንጸባርቀውን እልልታ ትርጉሙን እየጠየቁ በየራሳቸው ቋንቋ ለየመንግስታቸው በመላክ በሊቃውንቶቻቸው ያስመረምሩት ነበር። ተከታይና አጃቢ በመሆን የመጡትም ከቅኝ ገዥዎቻቸው ለመላቀቅ ለነበራቸው ምኞት ለምሳሌነት ይጠቅማቸው ዘንድ በህቡእ በሚያደርጉት እንቅስቃሴ ይነጋገሩበት ነበር።

አጎራባች አገሮችን ይገዙ የነበሩት ምዕራባውያን ቢችሉ ይህን ነጻብራቅ ለማዳፈን ባይችሉ ግን ወደ ጎረቤት አገሮች እንዳይሻገር ለመቆጣጠር የሚችሉበትን መንገድ ለመፍጠር ይጥሩ ነበር። የሞራል ሰዎች የሆኑት ፈረንጆች ግን የሚከተለውን ይመዘግቡ ነበር። ከብዙ ጸሐፊወች ውስጥ ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው።

፩ኛ. Rev Sterling M. Meaus” የተባሉ ጸሐፊ በ1945 ባቀረቡት መጽሀፍ። Ethiopia & the missing link in Africa history በሚል ርእስ “from time immemorial ethiopia has played an important part and often the leading role in the affairs of the world. The bible as well secular history conforms this fact.”(Page 100) ብለዋል።ህም ማለት ከጥንት ጀምሮ ኢትዮጵያ በዓለም ጉዳይ እጅግ የተደነቀ የሰው መሆንን ምሳሌነት መሪ የሚሆን ሚና ተጫውታለች”።

በሳቸው አገላለጽ በተለይ “The bible as well secular history conforms this fact.” ያሏትን ሀረግ ብንመለከት፤ በ secular history (በዓለማዊው ታሪካችን) የተከሰተውን እንደ ጥምቀት የመሰሉ በዓሎች የተሸከሙት ሚዛናዊት ፍትህ (እኩልነት) ከኛ አልፎ ለነ ማንዴላ የደረሰላቸውን ነጻነት ለመግለጽ እና፤ ከዚያም ቀደም ብሎ በራሳቸው ህዝብ የተሳደዱትን ሙስሊም ዓረቦችን የመሲህ ሰዎች የተባሉት ኢትዮጵያውያን እጃቸውን ዘርግተው የተቀበሉበትን ጽድቅ ለማመልከት ነው።

፪ኛ Drusilla Dunjee Houston የተባሉ ደራሲም “wonderful Ethiopians of the ancient Cushite Empire“ በሚል ርእስ ባዘጋጁት መጽሀፍ “from remotest times to the present , the Ethiopians have been the most celebrated and yet the most mysterious of nations.”(24) ብለዋል። ማለትም፦ ከጥንት ጀምሮ እስካለንበት ዘመን ኢትዮጵያውያን በታሪካቸው እጅግ የተከበሩ እጅግም የረቂቁ ናቸው” ብለዋል።

፫ኛ Iris Habib el Masir የተባሉ የኮፕቲክ ቤተ ክርስቲያንን ታሪክ ጸሐፊም አስደናቂ ምስክርነት ሰጥተዋል። ከሊቃውንቱ አንዱ ኢትዮጵያዊ ሊቅ በጥምቀቱ በዓል የሚደረገውን የጎልማሶችን ጭፈራ በምእራፍ ፲፰፡፯_፲ ከሰፈረው ከነቢዩ ኢሳይያስ ትንቢታዊ ምንባባ ጋራ በማነጻጸር ያቀረበውን ቅኔ በመረዳት “The true story of Christianity in Egypt 1982 ብለው በጻፉት መጽሀፋቸው ላይ “the sheep of Ethiopia have been delivered from the hayenas of the west by the doctrines of the Apostles and St. Cyril “(page 262) ብለዋል። ማለትም፦እንደተራበ ጅብ ዓለምን በመብላት ላይ ከነበሩት ምዕራባውያን ጅቦች ኢትዮጵያውያን የዳኑት በቅዱሳን አክትቪስቶች በነ ቅዱስ ቄርሎስ ትምህርት ነው።” ብለዋል።

ነቢዩ መሀመድም፤ ተከታዮቻቸውን ዓረቦች የራሳቸው ወገኖች ባሳደዷቸው ጊዜ “ክርስቶስ በተጠመቀ ጊዜ ያወጀውን ጽድቅ ለመፈጸም የሚጥሩትን የኢትዮጵያውያንን ዝና በመስማት ወደ ኢትዮጵያ ሂዱ ብለው ሸኝተዋቸዋል።

ነቢዩ መሀመድን ካነሳሁ ዘንድ፤ ባንድ ወቅት ዓረቦች ተናገሩ ተብሎ ተጽፎ ባጋጣም አግኝቼ ያነበብኩትን አለመመስከር ስህተት ስለሆነ አላልፈውምና ያንባቢን ትእግስት በመማጸን አቀርበዋለሁ።

ሴንት ሉስ እያለሁ በጣም የማከብራቸው የኮፕቲክ ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ Father Baslios የሚባሉ ቄስ ነበሩ። ከእለታት አንድ ቀን ልጎበኛቸው ከመኖሪያ ቤታቸው ሄድኩ። በተቀመጥቁበት ወንበር ሆኜ በፊቴ ያለውን ጠረጴዛ ስመለከት በጠረጴዛው ላይ በአረበኛ እና በእንግሊዘኛ ዓረብ አገር ተዘጋጅቶ የተላከላቸውን መጽሄቶች ሳገላብጥ፤ እሳቸው አዩኝና “የራስህ አገር መንግሥት የሚያደርገውን በውስጡ ታገኛለህ” አሉኝ፤ ውስጡን ሳገላብጥ እነ አቶ መለሰ ያደረጉትን ደባ ተጽፎ አነበብኩ።

ታሪኩ እንደዚህ ነው፤ እነ አቶ መለሰ ከኢትዮጵያ ጋራ በሚዋጉበት ወቅት “በናንተ ሙሉ እርዳታ አሸንፈን ኢትዮጵያን ከተቆጣጠርን ኢትዮጵያን የዓረብ ሊግ አባል የምትሆንበትን ህግ አውጥተን እናውጃለን” እያሉ ለዓረቡ ዓለም ቃል ገብተው ኖሮ፤ እንደተመኙት ሆነላቸው እና፤ እንደገቡ ያውጃሉ ብለው እነ አቶ መለሰን ቢጠብቁ ዘገዩ ባቸው። “ለምን ዘገያችሁ ? ብለው እነ አቶ መለሰን ዓረቦች ጠየቋቸው።

እነ አቶ መለሰ የሰጧቸው መልስ “በአገር አንድነት ህዝቡን አስተሳስራ የኖረችውን ቤተ ክርስቲያን ሳናዳክማት፤ በብሄራዊ ወኔ ያስተሳሰረችውንም ህዝብ በመከፋፈል ኃይሉን ሳናፈርሰው ልናውጅ ብንሞክር ለህልውናችን አዳጋች ስለሆነ ጊዜ ስጡን፤ ይልቁን በኢትዮጵያ ያሉት ሙስሊሞች ባለፈው መንግስት እየተገደድን የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ መቅደስን ህንጻ ሰርተናልና እኛም ገብተን እንጸልይ እንዲሉ ግፏቸው። እኛም መብታቸው ነው በማለት እስከ በመፍቀድ ድረስ እንገፋለን። በዚህ ሁኔታ ቤተ ክርስቲያንንም ህዝቡንም ካዳከምን በኋል እናውጃለን እንጅ፤ አሁን ብናውጅ እንዳሰብነው አይሆንም” ብለው መልስ እንደሰጧቸው ይገልጻል። ዓረቦች ይህን ታግሰው ከመቀበል ይልቅ በጣም ቸኮሉና፤ እነ አቶ መለሰን ለመርዳት ታጥቀው የሚገቡበትን መንገድ ተሰብስበው ሲነጋገሩ፤ ያካባቢው ሽማግሎች “ነብያችን ሀበሾች እውነተኛ የመሲህ ሰዎች ናቸው እና እንዳትነኳቸው ብለው አዝዘውናል። ቀን ጥሏቸዋል ብለን ይህን የመሰለ ደባ በአበሾች ላይ መፈጸም ከአላህ ጋራ መጋጨት ነውና አቁሙ” አሏቸው።

እነ አቶ መለሰን ለመርዳት ታጥቀው ለመግባት የፈለጉት ዓረቦች “አሁን በኢትዮጵያ ምድር ያለው አበሻ በነቢዩ ዘመን እንደነበሩት የመሲህ ሰዎች አይደሉም። ወደ ፈጣሪ አልባ እምነት ተለውጠዋል። ግማሹ በመስቀል ጦርነት ጊዜ ወደወረረን ክርስትና የተገለበጡ ናቸው ብለው እነ መለሰ ነግረውናል” ብለው እንደመለሱላቸው እና፤ ሽማግሎችም ”ምንም ይሁኑ በሀበሻ ምድር ላይ ካሉ እንዳትነኩ” ብለው አስቆሟቸው” የሚል በመጽሄቱ ላይ ተመዝግቦ አነበብኩ።

ኢትዮጵያውያን ሆይ! መጀመሪያ “ከረድችሁን እና አሸንፈን ኢትዮጵያን ከተቆጣጠርን ኢትዮጵያን የዓረብ ሊግ አባል የምትሆንበትን ህግ አውጥተን እናውጃለን”ማለታቸውን፤ ሌላ ጊዜ ደግሞ “በአገር አንድነት ህዝቡን አስተሳስራ የኖረችውን ቤተ ክርስቲያን ሳናዳክማት፤ በብሄራዊ ወኔ ያስተሳሰረችውንም ህዝብ በመከፋፈል ኃይሉን ሳናፈርሰው ልናውጅ ብንሞክር ለህልውናችን አዳጋች ስለሆነ ጊዜ ስጡን ማለታቸውን፤እስከዚያ ግን የኛን እቅድ በማራመድ እንዲረዱን በአገራችን ያሉት ሙስሊሞችን በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ መቅደስ እኛም ገብተን እንጸልይ እንዲሉ ግፏቸው” ማለታቸውን ስንመለከት፤ የዓረቡን ዓልም ሳይቀር በማታለል ኢትዮጵያን ለማፍረስ እነ አቶ መለሰ ያለ የሌለ አራዊታዊ ባህርያቸውን በግልጽ እንረዳለን። በበኩሌ ይህ እየዘገነነኝ ሳለ፤ አሁን በቅርቡ ደግሞ እነ አቶ መለሰ የዘረጉትን ህገ አራዊት ዶክተር አረጋዊ በርሄ፦

> *“የትግራይ ህዝብ ነጻ አውጭ ግንባር በ1979 አመተ ምህረት አስተሳሰብ ለዋጭ የፕሮፓጋንዳ መርሀ ግብር ለሚመለምላቸው ቀሳውስት ዘረጋ። የማሰልጠኑ ዓላማ ቤተ ክርስቲያኗን ከህዝብ ለይቶ በመምታት ስፋቷን ማጥበብና በትግሬአዊነት ላይ ብቻ የተመሰረተ ስሜት በትግራይ ተወላጆች ጭንቅላት መክተት ነው። ቤተ ክርስቲያኗ ለረዥም ዘመናት በህዝቡ አዕምሮ ላይ ስትተቀርጸው የኖረችውን ብሄራዊ የኢትዮጵያነትን ስሜት ከትግራይ ህዝብ አዕምሮ ጠራርጎ በጠባቡ ትግሬአዊነት ስሜት በመተካት የቤተ ክርስቲያኒቱን ይዘት እያጠበቡ ራሷን ቤተ ክርስቲያኒቱን መምታት ነው”* ብለው የገለጹትን ጽሁፍ አግኝቸ አነበብኩ። ታዲይ የኔ ቢጤ የቆሎ ተማሪ ጭንቅላት እንደሰረዝ ቅኔ የተደራረበውን የነ ገብረ ኪዳን ደስታን ህገ አራዊት እንዴት እና በምን መንገድ ሊገልጸው ይችላል?

በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ መነኮሳትና ሰባኪዎች መስለው ሰርገው ገብተው የነገብረ ኪዳንን አራዊታዊ ተልኮ የሚያራምዱትን በግልጽ እስካየሁ እና የዶ ክተር አረጋዊ በርሄን ጽሁፍ አግኝቼ በማንበብ እስካረጋገጥኩ ድረስ፤ በኮፕቲክ ቤተ ክርስቲያን ካገኘሁት መጽሄት ያነበብኩት ሰመመን ይሁን ይሁንብኝ እንጅ፤ በጣም አልከከነኝም ነበር። የነ ፋሌቅ ወጥመድ በሚል ርእስ ሰኔ ፳፻፩ ዓ.ም. ያቀረብኩትን ጦማር ይመልከቱ።

# መደምደሚያ

ይህች ጦማር ደርሳችሁ የምታነቡ ወገኖቼ! በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ያላችሁ፤ በኛ በካህናቱ ድካምም ይሁን በተለያዩ ምክንያቶች ከተጠመቃችሁባት እናት ቤተ ክርስቲያናችህ ርቃችሁ ያላችሁ፤ በእስልምና እና በኦሪቱ እምነት ያላችሁ፤ በህገ አራዊት ስብከት (ስብቀት) የተሰበቃችሁ የዚያ የዚህ ጎሳ አካል ነን ብላችሁ ሌላውን የጎረጥ በመየት ላይ ያላችሁ፤ በተለያዩ ርእዮተ ዓለማት ተከፋፍላችሁ በጎረጥ በመተታተት ላይ ያላችሁ።

በዮዲት ዘመን፤ ከዚያም በግራኝ መሀመድ ዘመን የተደረገውን የዘር መወራረስ፤ ከዚያም በመሳፍንቱ ዘመን በተደረገው አንዱን ሌላውን በመማረክና በፈቃድ በተደረገ መወራረስ ሁላችንም የተቀላቀልን መሆናችንን እና ያንድ ጎሳ ውጤት አለመሆናችንን ለማሳየት ያቀረብኩትን ሙከራ በጥሞና እንድትመለከቱት፤ እኛ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ተከታዮች ወገኖቻችሁ ክርስቶስ በጥምቀቱ ያወጃት ጽድቅ በልባችን ተተክላ በጽርሀ አርያም ያለች መሰላላችን ናት ብለን ብናምንም፤ ይህ እምነታችን እንደለ ሆኖ፤ ለሰው ዘር የሚጠቅም ጽድቃን የታወጀበት የጥምቀት በዓል የሁላችን ኢትዮጵያዊነት የጋራ ቅርሳችንና መኩሪያችን ስለሆነ ለቅርስነቱ እንድንጠነቀቅለት በትህትና እጠይቃለሁ።

እኛን ያመነጩን ህዝብ በዚህ አይነት ምስቅልቅል ያለፈና ያለፈባቸውን ሶስቱን ህግጋት ማለትም ህገ አራዊት፤ ህገ ኦሪትና ክርስቶስ ያወጃትን ጽድቅ ተመልከተናል። በጨለማው ዘመን የጥንት አባቶቻችን በሰሩት ስርአት ጽላቱን ተሸክመው ወደ ወንዝ የሚሄዱበትንም ተረድተናል።

ይህ ስርአት ከተሰበሰቡት መጻህፍት በላይ ውድና ክቡር ቅርሳች እንደሆን እና አባቶቻችን ከመጻህፍት እጅግ የበለጠ ጥቅም እንዳለው ገልጸውልናል። ለማረጋገጥ፤ ሳያውቁ በስህተት አውቀው ብሸፍጥ በሚነጉዱ ሰዎች "መጻህፍት ይሰረቃሉ። በምስጥ ይበላሉ፤ በዝናብም ይደመሰሳሉ። ይቃጠላሉ፤ አንብቦ የሚረዳቸውም ከራሳቸው ካካቢያቸው እና ዓለም ከደረሰችበት ግንዛቤ ጋራ ማገነዝብ የሚችሉ ጥቂት ብቻ ናቸው። በዓላት ግን የሚከናወኑባቸውን በማየትና ስለ ምክንያቱ ሲወራም በመስማት ያልተማረውም  ህጻኑም በቀላሉ ይማርባቸዋል። በሸፍጠኞች አይሰረቁም፤  አይደመሰሱም። አይቃጠሉም። ምስጥ አይበላቸውም  ይላሉ።

በ University of Cambridge Social Anthropologist **የሆኑት** Dr. Paul Connerton **የተባሉ ሰው** "How societies Remember" (1989) **በሚል ርእስ በጻፉት መጽሐፍ፤ በዓላት ከመጽሐፍ ባላነሰ ሁኔታ  ማስታወሻ መሆናቸውን የተጠቀሙበት አገላለጽ የጥምቀትን በዓል ከሰሩልን ዓባቶቻችን ስሜት ጋራ መስማማቱ እጅግ ያኮራል ያስደንቃልም።**

Dr. Paul Connerton **የተባሉት እኒህ የትኩረት ሰው፤ ለብዙ ዘመናት በታላቅ ስሜት በህዝብ ሲከበሩ የቆዩ ጥምቀትን የመሳሰሉት በዓላት፤ ፊደል ባልቆጠረ ዜጋ ሁሉ ይነበባል። ሲከበር በሚያዩ ህጻናት አእምሮ ላይ የጥልቀቱ የስፋቱ ምስጢር እያደጉ ሲሄዱ  በ** Social memory, collective memory, individual memory, **በ** personal memory **እና በ**Cognitive memory **ውስጥ የበለጠ ስር ይሰዳል።" አሉ።**

በበዓላት ብልጭ የሚሉ ትዝታዎች ባምስቱ ህዋሳቶች በማየት በመስማት በመዳሰስ በመቅመስና በማሽተት  አማካይነት ገብተው የሚጎዘጎዙት በዓዕምሮ ብቻ ሳይወሰኑ በህዋሳቶቻችን ሁሉ ላይ ነው። ለበዓሉ  በሚዘጋጁት ምግባችን ልብሳችን ቋንቋችን ላይ ይሰፍናሉ።  በዘፈን በደስታና በሀዘን አዲስና ትኩስ ሆነው እንደገና ይቀሰሳሉ። ጠቅላላው ህዝብ በመላ ሰውነቱ በተጎዘጎዘው ትዝታ በመገፋት ጥምቀትን የመሰሉትን በአላት ለማክበር ከጥቂት ሳምንታት በፊት በስሜት ይንቀሳቀሳል። በቅርቡ የደመራው በዓል በዓለም ዓቀፋዊነት እንደተመዘገበ ሰምተናል።  ከደመራው በዓል ይልቅ፤ የጥምቀቱ በዓል ያዘለው ምሥጢር እኛን ይቅርና የሰውን ዘር ሁሉ የሚያካትት ነው። አባቶቻችን የሰሩትን ይህን አኩሪ ቅርስ  አንዳንድ ሰዎች ሳያውቁ በስህተት፤ እያወቁ በሸፍጥ አፈር ሊያለብሱት ቢሞክሩም፤ የነሱን ከንቱነት  ከማሳየት በቀር። ይህን ቅርስ የማይፈልገው፤ የማይሻውና የማያደንቀው ስለሌለ በዓለም ቅርስነት መመዝገቡ የሚቀር አይደለም።

ምዕራባውያን ክርስትናን የተቀበላችሁ ሁሉ ወገኖች ኢትዮጵያውያን ሆይ! ይህ ሊቃውንት አባቶቻችሁ የሰሩት እናትና አባቶቻችሁ ሲከተሉት የነበረው አሁንም ያለው የጥምቀት በአል የሚኮራበት እንጅ የሚታፈርበት አይደለም። ራሳችሁን ከዚህ አግልላችሁ ልጆቻቸውንም ለዚህ ባይታወር ከማድረግ ይልቅ ራሳቸሁን ፈትሹ፤ ለልጆቻችሁም አስተምሩት። ለታሪካቸው ለቅርሳቸው ባይታወር አድርጋችሁ አታሳድጓቸው። የደመራው በዓል ዓለም አቀፍ ከሆነ፤ የጥምቀት በዓል የማይሆንበት ምክንያት የለም። ለልጆቻቸሁ ሳታካፍሏት ዓለም ቢቀድማችሁ ልጆቻችሁ ማሰብ ሲጀምሩ ምንያህል እንደሚታዛቧችሁ አትርሱ። ራሳቸው ምዕራባውያን ከራሳቸው ጥቅም አንጻር በፍርሀትና

በማንኳሰስ የጎረጥ ቢያዩትም፤ ሚዛንን የተከተሉ ሊቃውንቶቻቸው ግን በብራቸው መስክረውለታልን ልናፍረበት አይገባም። ይልቁንም እንደ ደመራው በዓል የጥምቀት በአላችንም፤ ዓለም አቀፍ እንዲሆን በምናደርገው ጥረት ተባበሩን።

## በህዝባዊ አገልግሎት ላይ ያላችሁ ወገኖች ሆይ!

ኢትዮጵያን ከወደቀችበት ህገ አራዊት ለማውጣት በየበሩ ቆማችሁ በመታገል ላይ ያላችሁ ሁሉ! ኢትዮጵያውያን አባቶቻችን በዓለም ባለው የሰው ዘር ልብ ውስጥ የጻፉትን ቅዱስ ስርአት በመናቅ በመሸሽ የየራሳችሁን ጽድቅ ለመትከል አትሞክሩ። እነ አቶ መለሰ የተከሉትን ህገ አራዊት ከኢትዮጵያ ነቅሎ የሚጥለው ይህ በጥምቀቱ በዓል የምናንጸባርቀው ነው። ለኢትዮጵያ የሚዋጋላት ይህን ጽድቅ መርሆ በማድረግ የሚንቀሳቀስ ሰራዊት ነው። ይህን ጽድቅ ከአንበሳ የተረፈ ቅንጥብጣቢ ለቃቃሚዎች ቀርቶ፤ የሲኦል ደጆች የተባሉት ኃያላንም ሳያሸንፉት ዘመናት ማቋረጡን ልንረሳ አይገባም።

ከውጭ የወሰዳችሁን ጠቃሚ ትምህርት ክርስቶስ ባወጃት በዚህች ጽድቅ ላይ መስርቱት፤ ህዝባችሁንም በዚህ አንቀሳቅሱት ይህን ብታደርጉ ቅዱስ ጳውሎስ *"ዑቁ እንከ ርእሰክሙ በእንተ አንብቦ ወዘልፈ ሀሉ ባቲ። ወእመሰ ዘ ንተ ገበርከ ርእሰከሂ ታድኅን ወዘኂ ይሰምአከ (፩ጢሞ ፩፥፲፮)* ብሎ የተናገረው ይፈጸምላችኋል።

- ***<u>ሙስሊም ኢትዮጵያውያን ወገኖች ሆይ!</u> ነቢዩ*** *መሀመድ* የእምነት አባቶቻችሁን ወደ ኢትዮጵያ ሂዱ አምልጡ ብለው ሲሸኗቸው ከኢትዮጵያውያን ውጭ ክርስቲያን ነኝ የሚል በዓለም ስላልነበረ አይደለም። ንብያችሁ ይህን ያሉት በጥምቀቱ በዓል አማካይነት በመላ ኢትዮጵያ የሚካሄደውን የጽድቅ ነጸብራቅ በመስማታቸው ነው። ስለዚህ በእምነት ብንለያይም በተመሰቃቀለው ዘራችን አንድ መሆናችን ካለመዘንጋት ጋራ፤ የእምነት አባቶቻችሁ ተሰደው ሲመጡ የሥጋ አባቶቻችሁ ያቀፉባት ስለሆነች የጥምቀትን በዓል እንደ ቅርሳችሁ ልትጠብቋት ይገባችኋል።
-

እኛ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ወገኖቻችሁ፤ ሲሆን መሲህ ካወጃት ጽድቅ ዝንፍ እንዳንል፤ ካልቻል ደግሞ ያሬት ካወጀችው ሚዛናዊት ፍርድ በታች እንዳንወድቅ በርቱ እንበርታ ልትሉን ከፍተኛ እዳ አለባችሁ። እነ አቶ መለሰን ለመርዳት ታጥቀው የሚገቡበትን መንገድ ተሰብስበው ሲነጋገሩ፤ ያካባቢው ሽማግሎች <u>"ነብያችን ሀበሾች እውነተኛ የመሲህ ሰዎች ናቸው እና እንዳትነኳቸው ብለው አዝዘውናል። ቀን ጥሏቸዋል ብለን ይህን የመሰለ ደባ በአበሾች ላይ መፈጸም ከአላህ ጋራ መጋጨት ነውና አቁሙ" ብለው የዓረብ ሽማግሌዎች የተናገሩትን እስላማዊውን ያደራ ቃል ከናንተ ከወገኖቻችን የበለጠ እንደምንጠብቅ አትዘንጉ!።</u>

## *<u>በዚህ ዘመን ከኔ ጀምሮ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ውስጥ ያለን ካህናት፡-</u>*

*<u>መነኮሳት ሆይ!</u>* *መጻህፍቶቻችን የሚያውቋችሁ በገዳማዊ ኑሯችሁ ነው። በከተማ ኑሯችሁ አይደለም። "አርጋኖነ ዲያብሎስ እልያማስኑ ሕሊናተ ርቱዓተ"* የተባሉት በህገ አራዊት የሚመሩ ሰዎች በከተማ በገጠር ባሉት ክርስቲያኖች ላይ ስለሚፈጥሩት ቀውስ፤ ከገዳማችሁ ሳትወጡ እንድትጸልዩ ነው። (ሃይ ምዕ ፸፪፡፵_፵፩)

ጸሎታችሁ ከደመና በታች ሳይወድቅ ያለ አንዳች እንቅፋት ቅድመ እግዚአብሄር ሊደርስ የሚችለው *"መቅድመ ኩሉ ይርኀቁ ጸ ድቃን ወመነኮሳት እምአንስት ወኢይቅረቡ ኀቤሆን ወኢትናገሩ ምስሌሆን ወይርሀቁ እምኔሆን ከመ ኢያውስኦን ምንተኒ ግሙራ "( ምዕ ፳፥፯)* ለሚለው መመሪያችን ተገዥ ስትሆኑ ብቻ ነው።

እኛም ጸልዩልን ልንላችህ የምንችለው *"ወንህነሰ ንጽህቅ ለርእዮተ ገጽክሙ ፍስህተ ወለሰሚአ ዜናክሙ ወዜና ኩሎሙ መርዔትክሙ ቡሩካን ወዜና ኖሎትኒ እለ እምታህቴክሙ ይእቀቦሙ እግዚአብሄር በጸሎ ትክሙ ወመነኮሳትሂ እለ ውስተ ገዳማት ወአበው ቅዱሳን ወያብጽህ ለነ እግዚ"* በሚለው መመሪያ ጸንታችሁ መቆማችሁን ስናረጋግጥ ብቻ ነው።

*"አረጋዊ መንፈሳዊ"* የተባለው መጽሀፍም በመጀመሪያ ድርሳኑ ላይ *"መፍትውኬ ለሰብእ ይትአቀብ እምተአርኮ ደቂቅ። ከመ ኢይርኮስ ልቡ በህሊና ዝሙት"*ይላል። እንደገና "ፍናዌ መልእክት አርብዓ" በሚለው ክፍል ላይ *"ዕቀብ አዕይንቲከ እምርእየ ኩሉ ሕስው"* ካለ በኋላ *"እስመ ያነቅሀ ለፍትወትከ"* ይልና፤ *"ኢታፍቅር ሕጻነ"* ብሎ አክሮ ይናገራል። ይህም ማለት ሰው ከመነኮሰ በኋላ የተፈጥሮ ፍላጎቱን ሊገታ የሚችለው ከሴትና ከህጻናት አካባቢ በመራቁ ብቻ መሆኑን ነው። በሮማ ካቶሊክ የደረሰው ማስረጃ ይሁነን። ኦርቶዶክሳዊቷ መመሪያችን የምትደነቀው ሰባዊ ባህርይን ሳትደብቅ፤ ጽድቅን ሳትለቅ በዘረጋችው መመሪዋ ነው።

በኢሀደግ ዘመን ካለችው ቤተ ክርስቲያናችን መነኮሳት በቀር በከተማ በህዝብ መካከል የሚኖር መነኩሴ የለም። በጥጋችሁ ያሉትን ሌሎች ኦርቶዶክሳውያንን ጠይቁ። መነኮሳት ከበአታቸው ሊወጡ የሚገባቸው ምንኩስናን የጀመረው አባ እንጦስ ያደረገውን ብቻ ለማድረግ ነው።

*አባ እንጦስ ከሚሰቃየው ህዝብ መካከል ሆኖ ሥቃዩን ለመካፈልና ለማጽናናት ከገዳሙ ወጥቶ ወደ እስክንድርያ ከተማ ገባ። በህገ አራዊት ወደ ሞት የሚወሰዱትን ሰዎች ከፊታቸው ቀድሞ ከህገ አራዊት ወታደሮች ጋራ ተጋፈጠ። ከእስረኞች ጋራ ታሰረ። እስረኞችን በጸሎቱ እና በድፍረቱ አጠነከራቸው። በሱ ምክንያት እሱን በተከተሉት ካህናት መነኮሳት ላይ በህገ አራዊት የሚመራው መንግስት የሚያስፈፈራ የሞት ቅጣት አወጀባቸው። አንጦንስ ይህን ሲሰማ ቀጥ ብሎ በህገ አራዊት ወደ ፈረደው ዳኛ ሄደ።* "He declared in a thunderous voice before him that he would never forsake his children ,but would stand by them to the very end. To the believers who watched him speak "his appearance was like unto that of the Angel of Light. (Page 61) *ተብሎ ከተጻፈው ታሪክ እንደምንረዳው፤ በህገ አራዊት የሚመራው ማክስምያኖስ የተባለው ሰው ሊቋቋመው አልቻለም። በእንጦስ ተሸነፈ። እንጦንስ ሁሉን ካስተካከለ በኋላ ወደ ገዳሙ ተመለሰ። ህዝቡም በልቅሶ ወደገዳሙ ሸኙት ይላል።*

*አሁን ባለንበት ዘመን ከኛ መነኮሳት በቀር አንድ መነኩሴ ባሜሪካ ከተማ የለም። ምንኩስና በህገ አራዊት የሚታወጅ መከራ በህዝቡ ላይ ሲደርስ ህዝቡን በሰላማዊ ሰልፍ ለመምራት ካልሆነ በቀር በከተማ መኖር ቀርቶ መታየት የለባችሁም። ይህን ስል ምስክሬ መጻህፍት ብቻ አይደሉም። በመላ ኦርቶዶክሳዋያን የተመሰረቱት ገዳማትና በውስጥ የሚኖሩት መነኮሳትም እየመሰከሩ ናቸው።*

*በከተማ እንድትኖሩ ካልተፈቀደላችሁ፤ ግን ከገዳም መወጣት ያለባችሁ የህዝቡን ችግር በቅድሚያ ለመጋፈጥ ከሆነ፤ እስቲ አስቡት ! ለራሳችሁ ምቾት በሰራችሁት ዳስ ለመኖር እንጅ፤ ያላችሁበትን የከተማ ኑሯችሁን መጽሀፎቻችን ፈጽሞ አይቀበሉላችሁምና በአባ አጋግዮስ ላይ የደረሰበት እንዳይደርስባችሁ አስቡ!*

## • ካህናት

*ጴጥሮስ የክርስቶስን ዓላማ ረስቶ ከምድራዊ ነገር ጋራ አገናዝቦ ለመኖር በወሰነው ፍላጎቱ "አይድረስብህ" ባለ ጊዜ "ዘወር በል ከፊቴ  አንተ ሰይጣን" ቢባልም ይህን ተግሳጽ ለመስማት ዘገየ። እኛም ከየ አቅጣጫው የሚሰነዘርብንን ተግሳጽ ከመስማት ይልቅ የየራሳችንን ዳስ እየሰራን በመኖር ላይ ነን። ለጠቅላላዋ ቤተ ክርስቲያንና ለህዝብ አልቆንም። በጥምቀት የታወጀው ጽድቅ ይቅርና "አቻ ላቻ) ሚዛናዊ ፍርድ ተገፎት በህገ አራዊት እጅ በወደቀበት ጊዜ ብዙዎቻችን በካባችን ተጠቅልለን ተኛን። የዲሲ ህዝበ ክርስቲያን በቤተ መቅደስ ተገቢ ያልሆነ ነገር ተፈጸመ ሲባል መተባበር ቀርቶ ስህተቱን በተቃወሙት ሰወች መዘባበት ጀመርን። ታዲያ እኛ ነን የጥምቀቱን በዓል መምራት የምንችለው?*

*በህግ ጋብቻ ያለን ካህናት "ሚስቱን ልጆቹን እርሻን ያልተዎ ለኔ ሊሆን አይችልም" የተባልነው እኛ እንጅ መነኮሳት አይደሉም። ስለዚህ በህገ አራዊት የሚካሄደውን ደባ መቃወም እኛን አይመለከትም። የቤተ ሰብ ሀላፊነት አለብን በማለት ታላቋ ቤተ ክርስቲያናችን ስትናወጽ ወገን ሲንገላት በቤተ መቅደስ መደበቅ ቤተ መቅደሱን ማርከስ ነው። ቅዳሴውን ወደ መተዳደሪያነት ቀየርነው። ይህን ቤተ ክርስቲያናችን የምትቀበለው አይደለም።*

*መጻሕፍትን እንመልከት! "አሮን ነደቀ ምሥዋዐ አንጻሮ ወአየደ እንዘ ይብል በዓለ እግዚእ ጌሰም"(ዘጸ ፴፪፡፭) ከህገ አራዊት (እንስሳ) ባለመላቀቃቸው በእንስሳ  ምስል እግዚአብሔር ያልፈቀደውን ለህዝብ የማይጠቅም ባዶ በአል ለማድረግ ከተነሱት ጋራ አሮን ተባብሮ  የራሱን ምስል ተከለ "ይበልኡ ወይሰትዩ  ወተንሥኡ ይዝፍኑ ወይትዋነዩ(፴፪፡፯) በጽላቱ ላይ ከተጻፈው ፍትህ ርትእ ጋራ ተስማሚ ባልሆነ፤ ነገር ግን በሕገ አራዊት እየተገፉ ሥጋቸው የፈቀደውን እያደረጉ ጽላቱን ሊቀበሉ ሞከሩ። ጽላቱ ከሕገ አራዊት ጋራ አንድነት ስላልነበረው ከነሱ ጋራ አልዘለቀም። እንደዚሁ ሁሉ ለራሳችን መተዳደሪ እቅድ በመዘርጋት የህዝቡን ያገር ናፍቆትና ትዝታ በቤተ መቅደስና በአውደ ምህረቱላይ እንደ ክራር እየመታን የምንፈጽመው ለጣኦት ከሚደረግ ስህተት የራቅ አለመሆኑን ልንረዳ ይገባናል። ህዝብ ሲጎዳ ህዝቡ "ሰማይ ስሚ መሬትም አድምጭ" እያለ ሲጮህ ከህዝቡ በዘረፍነው ገንዘብ እየተንደላቀቅን ራሳችንን ከህዝብ ለይተን በቤተ መቅደስና በአውደ ምህረቱ ላይ በምናደርገው አገልግሎታ ብቻ ከህዝብ ለመገናኘት መሞከር በህዝብ ላይ መሳለቅ መሆኑን ልንገነዝብ ይገባናል።*

*ይህን እንድል ያስገደደኝ ዲሲ ላይ በተፈጠረው ስህተት፤ ችግሩን ለመፍታት ከየአጥቢያው ክርስቲያኖች መጥተው እኔም ተጋብዥ በተገኘሁበት የታዘብኩት ነገር ነው። በስብሰባው ላይ የተገኙት ምእመናን ከሰሙ ባካባቢው ያሉት ካህነት እነሱ ሳይሰሙ ቀርተው ነው? እንዲያውም  አለመሰልጠና በማያገባንም እንደገባን አድርገው የተገኘነውን የወቀሱንና የሳቁብንም ገጥመውኛል። እነዚህ ሰዎች የነሱ መብት ሲነካ ቤተ ክርስቲያን የምትለውን በመጣስ ወደ ፍርድ ቤት የሄዱ ናቸው። ታዲያ በኛ ላይ የተሳለቁና የቀለዱ ካህናት "ኢትኅበሩ ምስለ እለ አልቦሙ ፍሬ ምግባሮሙ ዘጽልመት ኩለንታሆሙ። አላ ገስጽዎሙ። እስመ በዘ ጽሚት ይገብሩ ኀፍረተ ለነጊር" ኤፌ ፭፡፲፩ የሚለውን እንኳን ያነበቡ ሲነበብ የሰሙ ናቸው ማለት ያስችላልን? ይህ ጠባይ ያለን ካህናት መገሰጸ  የለብንምን? እሁድ እሁድ ከሰማይ የወረድን ቅዱሳን መላእክት መስለን ንስሀ ግቡ! እያልን የምንናገረው ለዳቧችን እንጅ ህዝቡን ለንስሀ ለማዘጋጀት እንዳልሆነ ግልጽ አይደለምን? ይልቅስ ይህ ህዝብ ከሰመመኑ ነቅቶ  ዲዮቅልጥያኖስ በአባ አጋግዮስ ላይ እንዳደረገው የምንወደውን ወርቅ አቅልጦ እስኪግተን ድረስ አንጠብቅ።*

- ***ምእመናን***

በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የተጠመቃችሁ አሁንም እምነታቸውን ጠብቃችሁ ያላችሁ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ሆይ! የበዓሉን ምሥጢር ላካባቢያቸው እያካፈላችሁ ክርስቶስ በጥምቀቱ ካወጃት ጽድቅ ላይ ለመድረስ ከጥንት ጀምሮ በመታገል እንደኖሩት አባቶቻችሁ የጥምቀትን በዓል በከፍተኛ ስሜት በያላችሁበት በየደረሳችሁበት አክብሩት።

በበዓላት ብልጭ የሚሉ ትዝታዎች ባምስቱ ህዋሳቶቻችን በማየት፣ በመስማት፣ በመዳሰስ፣ በመቅመስና በማሽተት አማካይነት ገብተው በዓዕምሮ ብቻ ሳይወሰኑ በህዋሳቶቻችን ሁሉ ላይ ተንዝሩዘዋል። ለበዓሉ በምናዘጋጃቸው ምግባችን ልብሳችን ቋንቋችን ላይ ይሰፍናሉ። በዘፈን በደስታና በሀዘን አዲስና ትኩስ ሆነው እንደገና ይቀሰቀሳሉ። ጠቅላላው ስሜታችን በተንዘንዘው ትዝታ ብቻ ሳይሆን በተሸከመው ቁም ነገር ጥምቀትን ለማክበር በስሜት እንቀሳቀስ!

በትዳር ህለፊነት ተጽእኖ በዓላቱ እንዴት ለምን እና በማን እንደተጀመረ ቁም ነገሩን አንርሳ። በትዳር ተወስኖ ልጅ በማሳደግ መኖር በዓል የተሸከመውን መልእክት ለመረዳት መጋረጃ ይሆናል። የተጀመረበትን ዓላማ እና ምሥጢር ያስለቅቃል። ይዘቱንና ጥቅሙን ለመረዳት እንድንጥር ከማድረግ ይልቅ በሰመመን ውስጥ ይከተናል። ግልብ ወደ ሆነ ስሜት በመነተት በዓሉን ለማክበር በሚደረገው ሽር ጉድ ላይ ብቻ እንድናተኩር ያደርገናል። ከዚህ ደረጃ ላይ ከደረሰን በሰመመን የምናከብራቸው በዓላት ለራሳችን ከሚሰጡን ጥቅም ይልቅ በራሳችን ላይ የሚያስከትሉብን ጉዳት እጅግ ይከብዳል።

በረፈ፣ “በጸህክሙ ኀበ ጽዮን ሀገረ እግዚአብሄር ህያው እንተ በሰማያት መንፈሰ ጻድቃን ፍጹማን”(ዕብ ፲፪፡፳፪—፳፬) “ፍጹማን የሆኑ መንፈሰ ጻድቃን ከሚኖሩባት ከእግዚአብሔር ከተማ ደርሳችኋል እንዳለው” ሕገ አራዊትንና ሕገ ኦሪትን ሰንጥቃ የወጣች በክርስቶስ የታወጀች ይህች ጽድቅ በክርስቲያኖች ልብ ተተክላ ማፏ በሰማይ ባለችው ከተማ ዘልቃ የገባች የእግዚአብሔር መከዳ መሆኗን እየገለጽኩ (ራዕ ፲፩፡፲፱)፣ ይህች ጽድቅ ከልባችን እንዳትነቀል እግዚአብሄር ይጠብቅልን እያልኩ፣ ለከርሞ ካደረሰን እንደ ደመራው በዓላችን በዓለም አቀፍነት ተመዝግባ የሰው ልጅ ሁሉ የሚሳተፉት እንድትሆን ለማድረግ ያባቶቻችንና የናቶቻችን አምላክ ይርዳን። በማለት እሰናበታችኋለሁ።

**ለሌሎች ቀሲስ አስተርአየ ጽጌ ጦማሮች የሚከተለዉን ድህረ-ገጽ ይመልከቱ::**

http://www.medhanialemeotcks.org/